በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡- 207081

ቀን፡-28/03/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካቾች ፡- 1ኛ አቶ ግርማ ገብራይ } ተወካይ አቶ ሽመልስ ገብራይ

2ኛ አይናለም ገብራይ }

3ኛ ሽመልስ ገብራይ- ቀረቡ

4ኛ ግዛቸው ገብራይ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ወሰኔ ገብራይ- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ የውርስ ክርክርን የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካቾች በኦሮሚያ ክልል ሻሸመኔ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ተጠሪ የእናታችንን እና የአባታችንን የውርስ ይዞታ አዋሳኞቻቸዉ በክሱ ይዘት የተጠቀሱትን በአራት ቦታ የሚገኙ የእርሻ መሬቶችን እንዲሁም በሻሸመኔ ከተማ ዉስጥ በ2000 ካሬ ሜትር ላይ የሚገኝ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰ መኖሪያ ቤት በጋራ እያስተዳደሩ ቆይተዉ ተጠሪ ድርሻችንን ሊያካፍሏቸዉ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ በመግለጽ ድርሻቸዉ እንዲያካፍሏቸዉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ አመልካቾች የዉርስ ሀብት ነዉ የሚሉት መሬቶች ከ1980 ዓ/ም ጀምሮ በግላቸዉ ይዘዉ የሚጠቀሙበት እንደሆነ መኖሪያ ቤቱንም በግላቸዉ የሰሩት እንደሆነ በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡እንዲሁም የዉርስ ንብረት በአመልካቾች እጅ እንደሚገኝ በመግለጽ አመልካቾች እንዲያካፍሏቸዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የሻሸመኔ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነዉ በሚል ክሱን ዉድቅ በማድረግ ዉሳኔ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም አመልካቾች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ ዉሳኔዉ ተሽሮ የዉርስ ሀብት ናቸዉ የተባሉትን ንብረቶች ግራ ቀኝ አብረዉ ሲጠቀሙ የነበረ መሆን አለመሆኑን በማስረጃ አጣርቶ በይርጋ መቃወሚያዉ ላይ ዉሳኔ እንዲሰጥ ለወረዳዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መልሶለታል፡፡የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 59200 የሆነዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ በቀን 09/07/2011ዓ/ም በሰጠዉ ብይን የእርሻ መሬቶችን በተመለከተ በጋራ ሲጠቀሙ እንደነበር ተረጋግጧል በማለት የይርጋ መቃወሚያዉን ዉድቅ በማድረግ መኖሪያ ቤቱን በተመለከተ ግን ተጠሪ ብቻቸዉን ሲጠቀሙ እንደነበር ተረጋግጧል በማለት በተጠሪ የቀረበዉን የይርጋ መቃወሚያ ተቀብሎ ከመኖሪያ ቤቱ አንጻር የቀረበዉ ክስ በይርጋ ታግዷል ሲል ወስኖ ከእርሻ መሬቶች አንጻር መዝገቡን መርምሮ ተገቢዉን ትእዛዝ ለመስጠት ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡በመቀጠልም የእርሻ መሬቶቹ የተጠሪ የግል ይዞታዎች ሳይሆኑ ለግራ ቀኙ በዉርስ የሚተላለፈዉ የወርስ ሀብቶች ናቸዉ በማለት ተጠሪ እንዲያካፍሏቸዉ በማለት በቀን 06/10/2011ዓ/ም ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች መኖሪያ ቤቱን በተመለከተ በተሰጠዉ ብይን ላይ ይግባኝ ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት በቀን 11/11/2011ዓ/ም ሲሆን ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 40491 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 05/05/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ አመልካች ይግባኝ ያቀረቡት ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ነዉ በሚል ያቀረቡትን ክርክር አመልካቾች ይግባኝ ማቅረብ የሚችሉት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320/3 መሰረት የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ከሰጠ በኋላ በመሆኑ የአመልካቾች ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ አላለፈም በማለት ዉድቅ ካደረገ በኋላ የአመልካቾች ዳኝነት ጥያቄ የዉርስ ሀብት ክፍፍልን የሚመለከት በመሆኑ በሰ.መ.ቁጥር 44025 ላይ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረት አመልካቾች የመኖሪያ ቤቱን ተጠሪ እንዲያካፍሏቸዉ ያቀረቡት ክስ በይርጋ አልታገደም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር ፍሬ ነገሩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

በመቀጠል ተጠሪ ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 325451 ላይ በቀን 22/04/2013 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካቾች መኖሪያ ቤቱን በተመለከተ በቀን 09/07/2011ዓ/ም በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የእርሻ መሬቶችን በተመለከተ ዉሳኔ እስከሚሰጥ ድርስ በጠበቅ ሳያስፈልግ ይግባኝ ማቅረብ ሲገባቸዉ ጊዜዉ ያለፈበትን ይግባኝ አቅርበዋል፤ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካቾች ማስፈቀጃ አቅርበዉ ሳይፈቀድላቸዉ ጊዜዉ ያለፈበትን ይግባኝ አለአግባብ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 320/3ን በመጥቀስ አከራክሮ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት አመልካቾች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡት ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ነዉ በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ ሽሯል፡፡አመልካቾች በዚህ

ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ችሎቱ በመ/ቁጥር 335862 ላይ በቀን 19/06/2013ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካቾች በቀን 03/09/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡-መኖሪያ ቤቱን በተመለከተ የቀረበዉ ዳኝነት ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል በማለት በተሰጠዉ ብይን ላይ ይግባኝ ማቅረብ የምንችለዉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 320/3 በተደነገገዉ መሰረት እና በሰ.መ.ቁጥር 116209 እና 89893 ላይ በተሰጠዉ ትርጉም ላይ በቀሪ ጉዳዮች ላይ ፍርድ ቤቱ እያከራከረ ጉዳዩ በቀጠሮ ላይ እያለ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ከሰጠ በኋላ ሆኖ እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካቾች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጊዜዉ ያለፈበትን ይግባኝ እንዳቀረብን አድርጎ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልን በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካቾች ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ንብረቱንም በውርስ እየተጠቀሙበት ባለበት ሁኔታ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ የተወሰበነት አግባብ ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 10/02/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልሳቸዉን ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- የክልሉ ሰበር በቀን 19/06/2013ዓ/ም ዉሳኔ ሰጥቶ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በቀን 30/09/2013ዓ/ም በ101ኛ ቀን ላይ በመሆኑ የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፎባቸዋል፡፡የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሳኔ የሰጠዉ አመልካቾች ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ያቀረቡት ይግባኝ ታይቶ መወሰኑ ስህተት ነዉ በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከመሻሩ ዉጭ በዋናዉ ጉዳይ ላይ በቀረበ የይርጋ መከራከሪያ ላይ ዉሳኔ ባልተሰጠበት ሰበር አጣሪ ችሎት ከይርጋ አንጻር በሰበር ችሎት እንዲመረመር ጭብጥ መያዙ ስህተት ነዉ፡፡አመልካቾች መኖሪያ ቤቱን በተመለከተ በቀን 09/07/2011ዓ/ም በተሰጠ ብይን ላይ ከሶስት ወር በኋላ በቀን 11/11/2011ዓ/ም ይግባኝ ማቅረባቸዉን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አረጋግጦ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጊዜዉ ያለፈበትን ይግባኝ ተቀብሎ አከራክሮ መወሰኑ ስህተት ነዉ በማለት በመሻር በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 320(2-4) ስር የተደነገገዉ መሰረት ያደረገ በመሆኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት መልሳቸዉን ሰጥተዋል፡፡አመልካቾችም በቀን 01/03/2014ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 251 መሰረት በመለወጥ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ጊዜዉ ያለፈበት ነዉ በማለት ሽሮ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካቾች በተጠሪ ላይ በወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ የወርስ ሀብት የሆኑትን በ2000ካሬ ሜትር ላይ የሚገኝ መኖሪያ ቤትና በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የእርሻ መሬቶችን ከተጠሪ ጋር አብረዉ እየተጠቀሙ እንደሚገኙ በመግለጽ ተጠሪ ድርሻቸዉን ሊያካፍሏቸዉ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ በመግለጽ ተጠሪ እንዲያካፍሏቸዉ እንዲወሰን ዳኝነት በመጠቅ ነዉ፡፡ተጠሪ ክሱ በይርጋ የታገደ ነዉ የሚል መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በማስረጃ ከመረመረ በኋላ በቀን 09/07/2011ዓ/ም በሰጠዉ ብይን አመልካቾች የመኖሪያ ቤቱን ከተጠሪ ጋር በጋራ መጠቀማቸዉን አላስረዱም በማለት መኖሪያ ቤቱን በተመለከተ የተጠየቀዉ ዳኝነት በይርጋ ታግዷል በማለት ዉድቅ በማድረግ የእርሻ መሬቶቹን በተመለከተ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶና መርምሮ በቀን 06/10/2011ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የዉርስ ሀብት ስለሆኑ ግራ ቀኙ ይከፈሉ በማለት የወሰነ ሲሆን አመልካቾች መኖሪያ ቤቱን በተመለከተ በተሰጠ ብይን ላይ ይግባኝ ያቀረቡት ይህንን ዉሳኔ ተከትለዉ በቀን 11/11/2011ዓ/ም በተጻፈ ይግባኝ ነዉ፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ በመቃወሚያዉ ላይ ብይን ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከታይ ይግባኝ የቀረበዉ ከ4 ወር በኋላ ሲሆን በፍርድ ቤቱ በመዝገቡ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከተቆጠረ ደግሞ ሁለት ወር ሳይሞላ አመልካቾች ለዚኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረባቸዉን ነዉ፡፡ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ነጥብ አመልካቾች ይግባኝ ማቅረብ ያለባቸዉ በመቃወሚያዉ ላይ ብይን ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 60 ቀን ወስጥ ነዉ ወይስ በመዝገቡ ላይ የመጨረሻ የፍርድ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ባሉት 60 ቀናት ዉስጥ ነዉ?የሚል ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በልዩ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የፍትሐ ብሔር ክርክር መመራትና እና እልባት ማግኘት ያለበት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት ነዉ፡፡ይህም ሥርዓት የተዘረጋበት ምክንያት ክርክር ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ወጭና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሁም ክርክሮች ተለይተዉ በሚታወቅ ሥነ ሥርዓት አግባብ ተመርተዉ ወጥነት ያላቸዉና እርስ በእርሳቸዉ የማይጣረሱ ፍተሐዊ እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ለማሳካት የታቀደዉ ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ነዉ፡፡የይግባኝ አቀራረብ እና ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ነዉ ተብሎ በሕጉ የተደነገገዉ ሥነ ሥርዓትም ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት በመሆኑ የሕጉን ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡በዚህ መሰረት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320(3 እና 4) ጣምራ ንባብ መሰረት ከሥረ ነገሩ ፍርድ በፊት በእጁ ያለዉን ንብረት ለሌላዉ ወገን እንዲያዘዉር የተሰጠ ዉሳኔ ካልሆነ በስተቀር በመጀመሪያ ደረጃ በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ በተሰጠ ጊዜ በሥረ ነገሩ ላይ የመጨረሻ የፍርድ ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በመቃወሚያዉ ላይ ብቻ በተሰጠ ብይን ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደማይቻል ተደንግጓል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ የክርክሩ ሥረ ነገር የዉርስ ሀብት ክፍያን መነሻ ያደረገ በመሆኑ የዉርስ ሀብት ከተባሉት ንብረቶች መካከል መኖሪያ ቤት በሚመለከት የተጠየቀዉ ዳኝነት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ አስቀድሞ ብይን የተሰጠ ቢሆንም የዉርስ ሀብት ናቸዉ ተብሎ በዚያዉ አንድ ክስ ላይ ዳኝነት በተጠየቀባቸዉ ሌሎች ንብረቶች ላይ ይህ ብይን በተሰጠበት ጊዜ የመጨረሻ የፍርድ ዉሳኔ ባለመሰጠቱ ጉዳዩ በቀጠሮ ላይ የነበረ መሆኑ ግራ ኙን ያከራከረ ጉዳይ ካለመሆኑም በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭም ይህንኑ ያሳያል፡፡

ስለሆነም አመልካቾች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የተሰጠዉን ብይን በቀሪዎቹ የዉርስ ሀብት በተባሉ ንብረቶች(ሥረ ነገሩ) ላይ የመጨረሻ የፍርድ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረባቸዉ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ክርክሮች ተጠቃለው ቀልጣፋ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ እንዲመሩና ከአንድ ሥረ ነገር ለሚመነጭ ጉዳይ የተለያየ መዝገብ እንዳይከፈት ለመከላከል በሚያስችል መልኩ ክርክሮች እንዲመሩ የታቀደዉን ዓላማ ከግብ የሚያደርስ የይግባኝ አቀራረብ በመሆኑ ሥነ ሥርዓት ሕጉ የዘረጋዉን ሥርዓት የተከተለ ነዉ፡፡በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካቾች ጊዜ ያለፈበትን ይግባኝ እንዳቀረቡ ገልጾ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር የወሰነዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320(3እና 4) ስር የተደነገገዉንና በዚህም ለማሳካት የታቀደዉን ዓላማ ከግምት ያላስገባ እና በሰ.መ.ቁጥር 116209፣ 185154 እና በተማሳሳይ በሌሎች መዛግብት ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 325451 ላይ በቀን 22/04/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 335862 ላይ በቀን 19/06/2013ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁጥር 325451 የሚታወቀዉን መዝገብ አንቀሳቅሶ ይግባኝ የቀረበበትን ጉዳይ መርምሮ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1 መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. በዚህ ዉሳኔ መሰረት እንዲፈጸም የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማነታወሸ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም